# "ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" መፅሐፍ፤ አል-አሙዲንን መጭረፍ ለምን አስፈለገው?

Wednesday, 25 February 2015 11:57

- በ ፋኑኤል ክንፉ



አቶ ገብሩ አስራት



ሼክ አልአሙዲ

ባሳለፍነው ሳምንት የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) የተመሰረተበትን 40 ኛ አመቱን ማክበሩ ይታወቃል። በዚህ በዓል ህወሓት ዳግም መደብ ውክልናውን ያደሰበት፣ የትግራይ ሕዝብም ለተጨማሪ ድሎች ከድርጅቱ ጋር ለመስራት ያለውን ዝግጁነት በይፋ ያረጋገጠበት መድረክ መሆኑን ከነበረው ሁኔታ መረዳት ይቻላል።

በበዓሉ ላይ የአብዛኛውን እድምተኛ ቀልብ የገዛው እና ወደኋላ ብዙዎችን የመለሰው፣ አብዛኛው የሰማዕታት ቤተሰቦች የተሰውቱን ልጆቻቸውንና ሌሎች የትግሉን ጓዶች ፎቶ ይዘው በመድረኩ ሲያልፉ ከታዳሚዎች መካከል በተለይ የቀድሞ ታጋዮች እያነቡ መቆም ያቃተቻውም ነበር። ወላጅ የራሱን አብራክ ክፋይ ሰማዕት ፎቶ አንግቦ እምባውን ዋጦ አድርጎ ለታዳሚው ለትግሉ ያበረከተውን ውድ የልጁን ህይወት ስጦታ ከፍ አድርጎ ሲያሳይ ምን ያህል ከባድ ኃላፊነት አመራሩ ላይ እየጫነ ስለመሆኑ ለመረዳት ልሂቃን መሆን አይጠበቅም።

በተለይ በነባሩም ሆነ በተተኪው አመራር ውስጥ አንዳንድ የተቀመጡበት ወንበር በጨረታ ከመደብር የተገዛ ለሚመስላቸው አመራሮች፣ ወላጆች የአብራክ ክፋይ ሰማዕት ልጆቻቸውን ፎቶ ከፍ አደርገው እንዲመለከቱ ሲያደርጉ ወይም ለታዳሚው ሲያሳዩ የተቀመጡበት የፖለቲካ ወንበር ከሕዝብ ልጆች አጥንት ደም የተሰራ እንጂ ከቀረሮ ወይም ከዋንዛ እንጨት የተሰራ ዘመናዊ ወንበር አለመሆኑን አስገንዝበዋል። አመራሩ ለማሕበራዊ ፍትህ፣ ለምጣኔ ሃብታዊ እና ለፖለቲካ እኩልነት እንዲሰሩ ከማሳሰባቸውም በላይ፤ በሕዝብ ወንበር ላይ ተቀምጠው የኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲካ ኢኮኖሚ በዚህች ሀገር እንዲሰፍን ታትረው ለሚሰሩ ፖለቲከኞችም የማንቂያ ደውል ሰማዕቱ መደወላቸውን እንዲገነዘቡ የተደረገበት መድረክ ነበር።

ሌላው ለዚህ በዓል ልዩ ድምቀት ከሰጡት አንዱ ሞሐ የለስላሳ መጠጦች ፋብሪካ ስምንተኛውን የለስላሳ መጠጦች ፋብሪካ በ 470 ሚሊዮን ብር ያስገነባውን በክብር ዶ/ር ሼክ መሐመድ ሁሴን ዓሊ አልአሙዲን እና በትግራይ ርዕሰ መስተዳድር በአቶ አባይ ወልዱ ተመርቆ መከፈቱ ነበር። ይህ አጋጣሚ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ወደ አቶ ገብሩ አስራት "ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" በሚል መጽሃፋቸው ስለ ክቡር ዶ/ር ሼክ መሐመድ ሁሴን ዓሊ አልአሙዲን

ኢንቨስትመንት ያቀረቡትን አስታውሶታል። ይሄውም፣ ሻዕቢያ ሼክ አልአሙዲን በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስትመንት እንዳያከናውኑ ያልፈነቀለው ድንጋይ አለመኖሩ በስፋት ዘርዝረው አስቀምጠዋል። አያይዘው ግን በሼክ አልአሙዲን ኢንቨስትመንት ላይ ያላቸውን የልዩነት ሃሳብ በምክንያት ማስደገፍ አቅቷቸው ወይም አልፈለጉ ይሁን የሼኩን ኢንቨስትመንት ጥያቄ ውስጥም ለመጣል ሞክረዋል። ሁለቱንም ከሳቸው ገለፃ እንመልከተው።

አቶ ገብሩ አስራት "ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" በሚለው መጽሃፋቸው ከገጽ 192 እስከ 195 ድረስ ያለውን ይህ ጽሁፍ በጭብጥነት አንስቶ ለመመልከት ይሞክራል። ይሄውም አቶ ገብሩ በግልፅ እንዳሰፈሩት፣ "ሻዕቢያዎች ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ራሷን ችላ እንድትበለጽግ" ፍላጎት አልነበራቸውም። አያይዘውም በ 1983 ዓ.ም. ክረምት ላይ ሻዕቢያዎች በጠሩት አገራዊ የልማት ኮንፈረንስ ላይ "ኤርትራ የአካባቢው የኢኮኖሚ አውራ ሆና እንደትበለጽግ የሚፈልጉ መሆናቸውን በይፋ ሲያውጁ ከተወሰነ ጊዜ በኋላም የሲንጋፖርን አርአያነት እንደሚከተሉ" በግልፅ ማስቀመጣቸውን አስፍረውታል። ይህን የኢኮኖሚ የበላይነት ስትራቴጂያቸውን ለማስፈጸም በቀንዱ ሀገሮች በተለይ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ሊኖራቸው ይችላል፣ እቅዳቸንንም ከግብ ለማድረስ እንቅፋት ሊሆን ይችላል ብለው እንደአንድ ስጋት የወሰዱት እንዲሁም በማንኛውም ዋጋ ሀገር ወዳድን ባለሃብት ሼክ መሐመድ ሁሴን ዓሊ አልአሙዲንን ለማጨናገፍ ወስነው እንደነበር የቀድሞ የትግራይ ክልል ፕሬዚደንት አቶ ገብሩ በመጽሐፋቸው አስነብበዋል።

አቶ ገብሩ በዚሁ መፅሐፋቸው "ሻዕብያዎች አልአሙዲን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያደርገው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ከፍ ብዬ የገልጽኩትን ስትራቴጂያቸውን የሚያበላሽ መስሎ ይታያቸው ስለነበር በበጎ አያዩትም ነበር" ብለዋል። አያይዘውም፣ "ሻዕቢያዎች አልአሙዲን ወደ ኤርትራ እንዲገባ በየአጋጣሚው ይወተውቱት ነበር። ኢሳያስ ከአልአሙዲን ጋር ለሶስት ሰዓታት ያህል ተነጋግሮ በኤርትራም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳደረገው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በኤርትራም እንዲያስፋፋ ጠይቆት ነበር። አልአሙዲ የኤርትራ ገበያ ምን ያህል ጠባብ እንደሆነ፣ የአገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ፖሊሲም ኢንቨስትመንትን እንደማይጋብዝ አሳምሮ ያውቅ ስለነበር ለሻዕቢያዎች ተስፋ ሊሰጣቸው አልቻለም። በወቅቱ የኤርትራ ሕዝብ ብዛት ሶስት ሚሊዮን እንኳን ካለመሆኑ በተጨማሪ የመግዛት አቅሙም በጣም ዝቅተኛ ነበር። አልአሙዲ በውይይቱ መጨረሻ አሁኑኑ በተጨባጭ የምትሸጡት ነገር ካላችሁ ልግዛችሁ ሲል አስመራ ውስጥ የተሻለ የሚባለውን ኒያላ ሆቴል በአምስት ሚሊዮን ዶላር ሸጠውለት ገንዘቡን ሰጥቷቸው ሆቴሉን ሳይረከብ ቀርቷል" ሲሉ ባለሃብቱ መዘረፋቸውን አስነብበዋል።

ሻዕቢያ በጠራራ ፀሃይ የሰውየውን ገንዘብ መዝረፉ ሳያንስ በኢትዮጵያ የሚካሄደውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ ሴራ ጠንስሰው ስሙን በማጥፋት ከኢትዮጵያ ሊያስወጡት ማሴራቸውን አቶ ገብሩ ጽፈውታል። በተለይ አቶ ገብሩ አፅንዖት በመስጠት ያስቀመጡት ፍሬ ነገር "ጉዳዩ እንዲህ ሲወሳ ቀላልና በሼክ አልአሙዲን ላይ ብቻ ያነጣጠረ ይምሰል እንጂ፣ መልዕክቱ ግን ከባድ ነው። ሻዕቢያ እንዲህ ዓይነት ቀሽም ድራማ ያቀናጀው በኢትዮጵያ ከፍተኛ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት እንዳይኖርና ኢትዮጵያን ሊያበልፅግ የሚችል ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዲገታ ለማድረግ እንደነበር ግልፅ ነው" ሲሉ የሻዕቢያን ሴራ አጋልጠዋል።

የሻዕቢያዎች ሴራ በዚህ አላበቃም ሲሉ አቶ ገብሩ ቀጣዩን በመፅሐፋቸው አስፍረዋል፣ "የኢሕአዴግ እና የህግዴፍ የጋራ ኮሚቴ በሚገኙበት ወቅትም ሻዕቢያዎች ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ በመምሰል የአልአሙዲን ጉዳይ በተለያየ መልኩ እንዲታይ ያቀርቡት" ነበር። አዛኝ መሳይ ቅቤ አንጓች እንዲሉ ሻዕቢያዎች "አልአሙዲንን ሙስና እያስፋፋ ነው" ሲሉ መክሰሳቸውን አውስተዋል። ሻዕቢያዎች ለዚህ አስተሳሰባቸው ያስረዳልናል ብለው ያቀረቡት ማስረጃ "አልአሙዲን ባለስልጣኖችን ማኖ በማስነካት ሙስና እያስፋፋ ነው" የሚል መሆኑን ጠቅለል አድርገው አስፍረውታል (በነገራችን ላይ በዚህ ጭብጥ ዙሪያ መከላከል የማይችሉ ግለሰብን ስም አንስተው ቢከሱም ስለማለታቸው ማረጋገጫ ብለው ያሰፈሩት ማጣቀሻ ግን መጽሐፉ ላይ

አላገኘሁም)። አቶ ገብሩ ወረድ ብለው ለዚህ ለተዛባና ለተዛነፈ የሻዕቢያየአዛኝ ቅቤ አንጓች አስተሳሰብ የተሰጠውን ምላሽ ሲያስቀምጡ፣ "…እኛ በዋናነት መቆጣጠርና ማጽዳት ያለብን የመንግስትና የፓርቲን መዋቅሮች እንጂ ባለሃብቶችን መሆን የለበትም" የሚል እንደነበር አስታውሰዋል።

በርግጥም አቶ ገብሩ በወቅቱ ይህን ሃሳብ ሰንዝረው ከሆነ ችግሮችን ስርዓት በማበጀት እንጂ ባለሃብቶችን ብቻ በማከም እንደማይፈታ ማመናቸው አንድ ነገር ነው። ሆኖም ግን የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአደባባይ የኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲካ ኢኮኖሚ የበላይነት እያገኘ መምጣቱን በይፋ ፓርላማ ቀርበው ማስረዳታቸው ይታወቃል። ከዚህ በላይ ርቀው ሄደው መንግስት በኪራይ ሰብሳቢዎች አንድ እጁን ታስሮ ነው የሚገኘው ሲሉ የአደጋውን ከፍታ ለሕዝብ አሳውቀዋል። ሌላው ቀርቶ የመቀሌ ነዋሪዎች ለጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ካቀረቡት ችግሮች አንዱ ኪራይ ሰብሳቢዎች የክልሉ አንዱ አደጋ መሆናቸውን ነው። በዚህ ክልል ውስጥ ይህን መሰል የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ አለ ተብሎ መስማት በጣም ከባድ ነው። ምክንያቱም አብዛኛው የክልሉ ሕዝብ ለትጥቅ ትግሉ ልጆቹን መስዋዕት አድርጎ መስጠቱ የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ በልጆቹ መስዋዕትነት ላይ የተቀመጡ አንዳንድ አመራሮች ለሚሰጡት መንግሥታዊ አገልግሎት ኪራይ አምጣ ሲሉት መስማት እንዴት እንደሚያም ሁሉም የሚገነዘበው ነውና።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲካ ኢኮኖሚ የስርዓቱ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ በታሪካችን የመጣንበት የፖለቲካ ኢኮኖሚ የኪራይ ሰብሳቢዎች ዋሻ መሆኑ የሚያሳይ ነው። ይህን መሰል የኪራይ ሰብሳቢዎችን የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ በማንኛውም መመዘኛ በዶ/ር ሼክ መሐመድ ሁሴን ዓሊ አልአሙዲን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ሊላከክ የሚችል አይደለም። በአሁን ሰዓት የተጋረጠውን የኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲካ ኢኮኖሚ በጠንካራ ስራዎችና በሕግ የበላይነት ብቻ ነው ማስወገድ የሚቻለው። አቶ ገብሩም በመጸሐፋቸው ላይ ሼክ አልአሙዲንን በተመለከተ እነእንትና እንዲህ ብለው ነበር፤ እኛ እንደዚህ አልን የሚሉት የአንድ ጊዜ መፍትሄ ቢሆን ኖሮ ዛሬም ባልተከተለን ነበር። ወይም አቶ ገብሩ በተሸራረፈ መልኩ ባለሃብቱን ለመግለጽ ከሚሞክሩ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ባለሃብቱ ምን እንደሚመስሉ ቢጽፉት አንባቢ የራሱን ድምዳሜ ይወስድ ነበር።

ሌላው አተያየታቸው አቶ ገብሩ በመጸሐፋቸው ላይ ባሰፈሩት ጽሁፍ ባለሃብቱ ላይ፣ ያላቸውን መገረም ይሁን ወይም የልዩነት ሃሳብ ወይም አንፃራዊ የባለሃብቱን ፍላጎት ለማሳየት አልያም እሳቸው በሚያውቁት አንድ ምክንያት ሃሳባቸውን ለማንፀባረቅ በዚህ መልኩ አስፍረውታል፣ "አልአሙዲ ከኤርትራ ይልቅ ኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት ማዕከል ለማድረግ የመረጠው የወላጅ እናቱን ሀገር ኢትዮጵያን የበለጠ ስለሚወድ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ መጠን ያለው መዋዕለ ንዋይ በኢትዮጵያ አፍስሶ፣ በርካታ የመንግስት የማምረቻ የንግድ ተቋማትን በርካሽ ገዝቶ፣ ወደፊት ሊያካብተው የሚችለውን ትርፍም አስቀድሞ አስልቶ ነው" ብለዋል።

ከላይ የሰፈረው የአቶ ገብሩ ሃሳብ ምን ለማስተላለፍ እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ከቢዝነስ ኤ..ቢ..ሲ… አንፃር ለትርፍ ብሎ ባለሃብቱ ኢትዮጵያን የመረጠው ማለታቸው ከሆነም ተፈጥሮያዊ ነው። ሆኖም ግን፣ ባለሃብቱ እሳቸው በሚሉት ቀመር አለመምረጡ እንጂ መምረጡ አስገራሚ አይሆንም። ማንም እንደሚያውቀው ማንኛውም ባለሃብት ለትርፍ እንጂ ለኪሳራ አይሰራም። ከሰራም ዓላማው ንግድ ሳይሆን ለሌላ እምቅ ፍላጎት ማራመጃ ተደርጎ የሚወሰድ ነው የሚሆነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ "የወላጅ እናቱን ሀገር ኢትዮጵያን የበለጠ ስለሚወድ ብቻ ሳይሆን" የሚል ሀረግ መጠቀማቸው በራሱ ምን ለማስተላለፍ ፈልገው እንደሆነ ግልፅ አይደለም። ከፃፉ "ውስጠ ወይራ" ከማድረግ ይልቅ በግልፅ ማስቀመጥ ነበር የሚጠበቅባቸው። በማንኛውም መመዘኛ ግን ባለሃብቱ ለወላጅ እናቱም ሆነ በሀገሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስትመንት ማድረጉን የመጀመሪያው ምርጫ ቢያደርግ ምን የተለየ ጥያቄ ሊያስነሳ እንደሚችል ግልጽ አይደለም።

ከዚህ ይልቅ አቶ ገብሩ ያላነሱት ወይም አውቀው ያለፉት በዚያን ጊዜ ባለሃብቱ ወደ ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ሲመጡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ቁመና በምን ዓይነት ደረጃ ይገኝ እንደነበር አላስቀመጡም? በወቅቱ የነበረውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ቁመናን ምንም ይሁን ምንም ባለሃብቱ አምነው ተቀብለው ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር አብረው ለመስራት መፈለጋቸው እንዴት አቶ ገብሩን እንዳላስገረማቸው ሌላው መነሳት ያለበት ጥያቄ ነው። እንዲሁም ራሳቸው አቶ ገብሩ የጠቀሱት የሻዕቢያን ሴረኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚያ ወቅት ኢትዮጵያ ትበታተናለች፣ ትበጣጠሳለች፣ ዘረኛ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ ነግሷል እየተባለ ከበሮ በሚደለቅበት ወቅት ባለሃብቱ ከእነ አቶ ገብሩ ጓዶች ጋር ሆነው ሀገራቸውን ለማቅናት መሰለፋቸውን አቶ ገብሩ እንዴት ጠፋቸው? የትኛውስ ባለሃብት ነው በአዲስ ስርነቀል የፖለቲካ አየር ውስጥ ሃብቱን የሚያፈሰው? ሁሉም ይቅር እና እርስዎም በስልጣን በነበሩበት ጊዜም ይሁን እስካሁን ድረስ ዓለማችን ካሏት በመቶዎች ከሚቆጠሩ ቢሊዮነሮች መካከል ምን ያህል የአለማችን ቢሊዮነሮች የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት መቀላቀል ችለዋል?

ምላሹን ለአቶ ገብሩ እንተወው። እሳቸው ያስቀመጡትን "ውስጠ ወይራ" ተቀብለን መሬት ላይ ያለውን እውነታዎች ስንመለከት እንኳን፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ኤጀንሲ በመባል የሚታወቀው መ/ቤት ከ 1987-2005 ዓ.ም. ድረስ በጨረታ አውጥቶ በድምሩ 206 ድርጅቶች ወደግሉ ዘርፍ ያዛወረ ሲሆን፣ ከነዚህ ድርጅቶች መካከል ሼክ አልአሙዲ 23 ያህል ድርጅቶች ለመግዛት ችለዋል። የቀሩትን ማን እንደገዛቸው ለማወቅ ወደ ኤጀንሲው ሄዶ ማረጋገጥ ነው። የባለሃብቱ ድርጅቶች ግን በአሁኑ በጠቅላላው ከ 70 በላይ ደርሰዋል። በእነዚህ በባለሃብቱ ድርጅቶች ውስጥ ከ 40 ሺ በላይ ሠራተኞች ተቀጥረው ይሰራሉ። መረዳት ለፈለገ ከተራ ትርፍ ማጋበስ ከፍ ያለ ኃለፊነት መሸከም ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ሌላው አቶ ገብሩ የሻዕቢያን ሴረኝነት ጨካኝነት ጠንቅቀው እንደሚያውቁ መጽሐፋቸውን ያነበበ የሚፈርደው ነው። በተለይ ሻዕብያ የእሱን ተቀናቃኝ የፖለቲካ ኃይሎችን በአራቱም የኢትዮጵያ ግዛቶች እየተወረወረ መግደሉን አስነብበዋል። ከዚህ በላይ ርቀው ሄደው ኢትዮጵያ ውስጥ ሻዕቢያ በዘረጋው የደህንነት መረብ ብዙዎችን አፍኗል፤ ረሽኗል። የዚህን አይነት የአገዛዝ ባሕሪ ያለውን ድርጅት ሳይፈሩ ሊያስከትልባቸው የሚችሉትን የተለያዩ አደጋዎችን ወደጎን አድርገው፣ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በወቅቱ ለመስራት ባለሃብቱ ሲወስኑና ወደ ሥራም ሲገቡ ከሻዕቢያ በኩል አንዳችም ጥቃት እንደማይደርስባቸው ኃላፊነት የወሰደው አካል ማነው? በተለይ የእሳቸው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የሻብዕያን የኢኮኖሚ ስትራቴጂክ ግብን ያናጋል ብለው አቶ ገብሩ ምስክርነት በሰጡበት መፅሐፍ መነሻ፣ ባለሃብቱ ሃብት ከማካበት ፍላጎት ባሻገር የባለቤትነት ምንም አይነት ስሜት ሳይኖራቸው ሻዕቢያ የደቀነባቸውን ሴራ ከምንም ግምት ሳያስገቡ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ውስጥ እንዴት ሊሳተፉ ይችላሉ ብሎ መውሰድ ይቻላል? ሻዕቢያ ከደቀነባቸው ሴራዎች ጋር ከመፈታተን በሌሎች በሽግግር ላይ ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ ባለሃብቱ ገብተው በሰላም መስራት ማንስ ከለከላቸው?

በአጠቃላይ ሲታይ አቶ ገብሩ የክብር ዶ/ር ሼክ መሐመድ ሁሴን ዓሊ አላሙዲን በመጸሐፋቸው ማንሳታቸው ካልቀረ ጨርፈዋቸው ከሚያልፉ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በማሳየት እሳቸውም ሆኑ ሌሎች አካሎች እንዲማሩበት ማድረግ ቢችሉ ምንኛ ጥሩ በሆነ ነበር።

ለአብነት ብዙ ስለሚባልለት ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃላ.የተ.የግ.ማ. የኢንቨስትመንት ፋይዳ እንመልከተው፣ የለገደንቢወርቅ ማዕድን ኩባንያ ግዥ ከ 1 ነጥብ 1 ቢሊየን ብር በላይ ወጥቶበታል። ኩባንያው ሚድሮክ ወርቅ ኃላ.የተ.የግ.ማ. ተብሎ እንደ አዲስ ሲመሠረት ሼህ ሙሐመድ ሁሴን ዓሊ አል-አሙዲ 80 በመቶ፣ ባለቤታቸው ወ/ሮ ሶፍያ ሳላህ አል-አሙዲ 18 በመቶ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የ 2 በመቶ የአክስዮን ድርሻ በያዙ ሦስት የአክስዮን ባለቤቶች በባለቤትነት የተያዘ ሕጋዊ የመመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ ያለው ኩባንያ ነው።

በሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ሥር ከሚገኙ ኩባንያዎች አንዱና ግዙፉ ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኩባንያ

መሆኑም የሚታወቅ ነው። እ.ኤ.አ በጁን 2000 ዓ.ም መነሻ ካፒታሉ 352 ሚሊየን 730 ሺህ 763 ብር የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ጠቅላላ ኢንቨስትመንቱ መጠን 1 ቢሊየን 845 ሚሊየን 639 ሺህ 323 ብር መድረስ ችሏል። 1 ሺህ 398 ያህል ሠራተኞችንም ያስተዳድራል።

የለገደምቢ ወርቅ ኢንተርፕራይዝ በፕራይቬታይዜሽን ወደ ሚድሮክ ወርቅ ከመተላለፉ በፊት እ.ኤ.አ ከ 1989-1997 ዓ.ም ይመራ የነበረው በመንግሥት ይዞታ ሥር ነበር። የለገደምቢ ወርቅ ማዕድን ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኤጀንሲ በግዥ ወደ ሚድሮክ እንዲተላለፍ የተደረገው እ.ኤ.አ በጁን 1997 ዓ.ም ነው። በተጨማሪም የማምረትና የወርቅ ፍለጋ ሥራውን የሚያከናውንበትን መመሪያ፣ ፈቃድና ቁጥጥር በሚመለከት ከማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር እ.ኤ.አ መጋቢት 29 ቀን 2998 ዓ.ም ስምምነት ተፈራርሟል። በዚህ ግዥ መሠረት የወርቅ ማምረት (mining) እና የወርቅ ፍለጋ (exploration) በደቡብ ኢትዮጵያ በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን አዶ ሻኪሶ ወረዳ ልዩ ስሙ ለገደንቢ በሚባል ሥፍራ እንዲሠራና ውጤታማ እንዲሆን አስችሎታል።

ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኩባንያ ወደ ሚድሮክ ከተቀላቀለበት ወቅት ጀምሮ የላቀና ጥራት ያለው የሥራ አፈፃፀም በማሳየቱና ለአገሪቱ በሚያስገኘው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከቀድሞው የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስና ከቀድሞው የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ እጅ ልዩ ልዩ ከፍተኛ ሽልማቶችን በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀበለ ሲሆን፤ ሽልማቶቹም ከሰባት በላይ ይሆናሉ። ኩባንያው በለገደምቢና በሳካሮ ከሚያካሂደው ወርቅ የማምረት ሥራ በተጨማሪ በወርቅ ፍለጋ (exploration) ሥራው በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል (ከታላቁ ህዳሴ ግድብ በቅርብ ርቀት) በመተከል ዞን 33 ሺ ኪሎ ግራም የወርቅ ክምችት ያገኘ ሲሆን፤ ይህን ክምችት የማውጣት ሥራ ሲካሄድ ለአገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ እንደሚሆን ይታመናል።

ሼክ አልአሙዲ በኢትዮጵያ ካሏቸው ከ 70 በላይ ድርጅቶች ለአብነት ያህል የተነሳው ከላይ የሰፈረው የኢንቨስትመንት አፈፃፀም ያለውን ሀገራዊ ፋይዳ ለማሳየት ነው። እንደ አቶ ገብሩ አገላለጽ ከተራ ትርፍ ፍለጋ ብቻ የሚመደብ ከሆነ የዓለም የኢንቨስትመንት ቲዎሪን ጥያቄ ውስጥ የሚጥል እንጂ ሌላ ትርጓሜ የለውም።